© Mercy Corps



# STRENGTHENING SOCIO-ECONOMIC DEVELOPMENT AND BETTER EMPLOYMENT OPPORTUNITIES (STEDE) COUNTERFACTUAL IMPACT EVALUATION

Funded by the European Union

## የግምገማ አውድ

ይህ ፕሮጀክት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳትፎዎ
ችን በማስተዋወቅ በኢትዮጵያ፣ ሶማሌ ክልላዊ መን
ግስት፣ ፋፋን ዞን ውስጥ የሚገኙትን የስደተኞች እና
ተቀባይ ማህበረሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ያለመ ነው። ፕሮ
ጀክቱ እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ከሜርሲ
ኮርፕ ጋር በመተባበር የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበ
ራት (VSLAs) እንዲቋቋሙ በማስተዋውቅ እና በመደ
ገፍ እንዲሁም ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባ
ራትን እያከናወነ ይገኛል።

በሜርሲ ኮር በ2022 በተደረገ  የመረጃ ክትትል
መሰረት በአውባሬ፣ ሸደር እና ቀብሪበያህ ባሉ የስደ
ተኛ መጠለያ ካምፖች ውስጥ 83 የመንደር ቁጠባና
ብድር ማህበራት የተመሰረቱ ሲሆን፤ አውባሬና ቀብ
ሪበያህ ባሉት ስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰቦች (host
communities) ውስጥ ደግሞ 188 ሚሆኑ ማህበ
ራት ተመስርተዋል። አንድ የመንደር ቁጠባና ብድር
ማህበር በአማካይ 20 አባላት ያሉት በመሆኑ ከስደ
ተኞች ውስጥ ወደ 1,660 የሚጠጉ ሰዎች እና ወደ
3,760 የሚጠጉ ተቀባይ ማህበረሰቦች በዚህ ፕሮግ
ራም ውስጥ ተሳትፈዋል።

## ለውጦችን/ተፅዕኖዎችን ስለመረዳት

የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራትን አስተዋፅኦ ለመ
ረዳት፣ C4ED የፕሮግራሙን ግምገማ እያካሄደ ነው።
በተለይም፣ C4ED RCT የሚባለወን የጥናት ዘዴ
ማለትም ፕሮግራሙን ለመጠም መስፈርቱን ያሟሉ
መንደሮችን፣ ተጠቃሚና እና ተጠቃሚ የማይሆኑ
(treatment & control) መንደሮች ብሎ በዘፈቀደ
(randomly) በመመደብ እና በአማካይ ተመሳሳይ እን
ዲሆኑ በማድረግ ጥናቱን እያካሄደ ነው።

ነገር ግን ይህ ፕሮግራም ስደተኞች ላይ ያሳደረውን
ተፅእኖ ለማጥናት፣ የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በዘፈ
ቀደ ስላልተመረጡ(ስለማይቻል)፣ C4ED የፕሮፐንሲቲ
ስኮር ማቺንግ (የማዛመድ) ዘዴን ይጠቀማል።

## እውነታው

**ተግባር ላይ የሚያውለው አጋር ሙሉ ስም**

ሜርሲ ኮርፕስ

**ክልል**

ሶማሊያ ክልል፣ ፋፋን ዞን, ኢትዮጵያ

**የአሰራር መንገድ**

ክላስተር Randomized Controlled  የሚደረግ
ሙከራ፣ የማዛመጃ (matching); የተቀላቀለ
አሰራር መንገድ (mixed approach)

**ጥናቱ የሚያካትተው**

ሴቶች፣ስደተኞች እና ስደተኞችን ተቀባይ
ማህብረሰብ,  ,

**የአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ መጠን**

10 000 000 EUR

የፕሮጀክቱን ተፅእኖ ለመመዘን፣ C4ED ፕሮጀክቱ
ከመጀመሩ በፊትና ፕሮግራሙ ከተጀመረ 17 ወር
በኋላ ከስደተኛ መጠለያ ካምፖች እና ከተቀባይ ማህ
በረሰቦች (host communities) ደግሞ 13 ወር በኋላ
ያለውን መረጃ ሰብስቧል።
የመነሻ(baseline) ዳሰሳ ጥናት ከ35 ቀበሌዎች ውስጥ
የተወጣጡ 70 መንደሮችን እና ከ3 የስደተኛ መጠለያ
ካምፖች ደግሞ 44 ብሎኮችን በማካተት በ2021 ሶስ
ተኛው ሩብ አመት ውስጥ ተካሂዷል። በድምሩ C4ED
ከ1,839 ሰዎች መረጃን ሰብስቧል። የቤዝላይን ዳሰሳ
ጥናቱ ዋና አላማ ጥናቱ ላይ ስለተሳተፉት ማህበረሰብ
የተሻለ እይታ እንዲኖር እና ከመነሻው የጥናት ከመ

ነሻው ጥናቱ ፕሮግራሙ ከመሰጠቱ በፊት የበፕሮግራሙ ጥናት ውስጥ የተሳተፉት ካልተሳተፉት ጋር በአማካይ ተመሳሳይ ባህሪያት እንዳላቸው ለማረጋግጥ ነው።

የመጨረሻው የዳሰሳ ጥናት(endline) የተካሄደው ከግንቦት እስከ ሰኔ 2023 ዓ.ም ሲሆን ከ1,822 ምላሽ ሰጪዎች መረጃ ተሰብስቧል። ከአሃዛዊ መረጃው በተጨማሪ C4ED ከ33 ዋና ዋና የመረጃ ሰጭዎች ውስጥ፣ 19 ቃለመጠይቆች፣  7 ጥልቅ ቃለመጠይቆች (indipth interview)፣ እና 7 የቡድን ውይይቶች (fucussed group interview) በማካሄድ  መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል።

# BUILDING ON SOLID FOUNDATIONS

ካውንተርፋክቱዋል ተፅዕኖ ግምገማ (Counterfactual impact evaluations) ፕሮግራሙ በተጠቃሚዎች ላይ የሚያመጣውን ትክክለኛ ለውጥ ለመለየት ያስችላል። ካውነተርፋቷል (counterfactual) ማለት ተጠቃሚዎቹ በፕሮግራሙ ባይሳተፉ ኖሮ ሊኖር የሚችለው ለውጥ ማለት ነው። ይህም ዘዴም ከፕሮግራሙ  በፊት እና በኋላ(before and after) ያለውን ለውጥ ከማነፃጸር በተሻለ ሁኔታ የፕሮግራሙ ለውጦችን ከሌሎች ለውጦች (ውጤቶች) ለመለየት ያስችላል። በፕሮግራሙ ባይሳተፉ ኖሮ ሊኖር የሚችለው ለውጥን በቀጥታ ማየት ስለማንችል የፕሮግራሙን ለውጦች ለመገመት እንዲያስችለውን ኤክስፐርመንታል እና ኳይዚ ኤክስፐርመንታል(experimental and quasi-experimental methods) ዘዴዎችን በመጠቀም በፕሮግራሙ የማይሳተፉ ሌሎች ተነፃፃሪዎችን እንለያለን።

ራንድማይዝድ ኮንትሮል ሙከራ (Randomized Control Trial)፣ ለፕሮግራሙ ከተምረጡት መሀል በዘፈቀደነት ሰዎችን በመምረጥ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ወይንም እንዳይሆኑ በማድረግ የሚሰራ የሙከራ አሰራር ነው። ይህ ዘፈቀዳዊነት በፕሮግራሙ ተጠቃሚ በሆኑት እና ባልሆኑት መካከል ያለውን ስልታዊ ልዩነት ያስወግዳል፤ ይህም ተመራማሪዎች ፕሮግራሙ የሚፈጥረውን ለውጥ እንዲገምቱ ያስችላቸዋል። ይህ አሰራር ለተቀባይ ህብረተሰቦች (host comminities) የሚሰራ ቢሆንም ግን ስደተኞች ላይ ስለማንከተለው ወደ ፕሮፐንሲቲ ስኮር ማቺንግ ቴክኒክን (የማመሳሰል ዘዴ) እንጠቀማለን።

ፕሮፐንሲቲ ስኮር ማቺንግ፡  ስደተኛ ተጠቃሚዎችን በዘፈቀደ መምረጥ ስለማይቻል ለዚህ ፕሮጀክት  የፕሮግራሙን ለውጥ ለመመዘን ወይም ለመለካት C4ED የራንድማይዝድ ኮንትሮል ሙከራን አይጠቀምም። በምትኩ፣ የ PSM ወይም የማዛመድ ዘዴን እንጠቀማለን፣ በፕሮጀክት ተሳታፊዎችን እና ያልተሳተፉትን በተቻለ መጠን በሚታዩ ባህሪያት (observable characterstics) ላይ ተመስርተው እንዲነጻጸሩ የሚያደርግ ስታቲስቲካዊ ሂደት ነው። በእነዚህ በሚታዩ ባህሪያት በማመሳሰል፣ ይህ የኳሲ-ሙከራ ዘዴ በፕሮጀክቱ ምክንያት የሚመጣን  ለውጥ ለማወቅና በሁለቱ (ተዛማጅ) ቡድኖች መካከል ውጤቶችን ለማነፃፀር ያስችላል።

## CIE ፖሊሲ እንዴት  ይጠቅማል?

የዚህ የግምገማ ጥናት ግኝቶች የVSLA መርሃ ግብር የታለመለትን ውጤት ማሳካት አለመሳካቱን፣ ለምሳሌ በምን ያክል ለፋይናንሺያል አቅም መሻሻል፣ ለማህበራዊ ትስስር፣ ለስራ ዕድል ፈጠራ እና ስደትን ለመቀነስ አስተዋጾኦ እንዳበረከተ ለአውሮፓ ህብረት የአደጋ ጊዜ ትረስት ፈንድ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለማሳዎቅ ይረዳል። ከዋጋ-ውጤታማነት እና አዋጭነት ትንተና የተገኙት ግኝቶችም መርሃ ግብሩ ወጪ ቆጣቢ እና ሊስፋፋ እንደሚገባው ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያሳውቃል።

## ለወደፊት የፕሮጀክት ትግበራ እና ግምገማ ጠቃሚ ምክሮች

- የአንድን ፕሮግራም ተጽኖ ወይም ውጤቱን ለማጥናት ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት RCT ማካሄድ ያለውን አንድምታና የሚፈሰውን መዋዕለ ንዋይ ለማስተካከል ያለውን ጥቅም ለሁሉም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለማሳየት ይረዳል።
- የፕሮጀክቱ ፈፃሚዎች የፕሮግራሙን ተግባራት እና የKPIዎችን ለውጥ ለመከታተል ደረጃውን የጠበቀ የክትትል ስርዓት እንዲከተሉ ይመክራል። ለዚሁ ዓላማ፣ እንደ Kobocollect፣ Survey Solutions፣ Survey CTO ወይንም CommCare ባሉ መሳሪያዎች አማካኝነት በዲጂታል የሚደረግ መጠይቅ ፎርም መጠቀም በጣም ይመከራል።

Center for Evaluation and Development

EUTF for Africa

This publication was produced with the financial support of the European Union.
Its contents are the sole responsibility of the Center for Evaluation and Development (C4ED) and do not necessarily reflect the views of the European Union.
© 2023 Center for Evaluation and Development. All rights reserved. Licensed to the European Union under conditions.